PO BOX 11699
TACOMA WA 98411-669

# የቃለ-መጠይቅ ቀጠሮ ለአመልካች
## Interview Appointment for Applicant

Washington State Department of Social & Health Services
Transforming lives

Date

TTY / TDD ቁጥር: 800-209-5446
ነፃ የጥሪ መስመር: 877-501-2233

Client's Name and Address

የደንበኛው መታወቂያ ቁጥር: Client ID

ውድ Client's Name :

ማመልከቻዎን የተቀበልነው በ Date . ቃለ-መጠይቁን ማጠናቀቅ ያለብዎት በ Date . በዚህ ሊደውሉልን ይችላሉ 877-501-2233 ወይም ቢሮ የምጡ። ከመንግስታዊ በዓላት ውጪ የቃለ-መጠይቅ ሰዓታችን ከሰኞ እስከ አርብ 8:00 a.m. እና 3:00 p.m. መካከል ነው።

ቦታዎች:

CSO Name and Street Address

ከእርስዎ ካልሰማን በ Date , ማመልከቻዎ ለ ☐ መሠረታዊ ምግብ (Basic Food) ☐ ካሽ (Cash) ሊከለከል ይችላል።

ያለ ቃለ-መጠይቅ ለእገዛ ጥያቄዎ ሊከለከል ይችላል።

**ይህ ዝርዝር ለቃለ-መጠይቅ ሊያስፈልጎ የሚችሉ ነገሮች ናቸው:**

- የሚያመለክቱለት ሰው ማህበራዊ ዋዋትና ቁጥር
- የዜግነት ማረጋገጫ ወይም ሕጋዊ ሰነዶች እንዴ አመርካ ፓስፖርት፣ ልደት ምዝገባ፣ የስደት ዶክመንቶች።
- የማንነት ማረጋገጫ እንደ የመታወቂያ ፎቶ
- የገቢ ማረጋገጫ እንደ ቼክ ኮፒዎች፣ ቀሪ ቼክ፣ ዴብዳቤዎች ወይም ለቤተሰብዎ ገንዜብ የሚሰጡ ከማናቸውም የሆነ ማረጋገጫ
- ሊኖሩት የሚችሉ ሀብትና ንብረቶች ማረጋገጫ እንደ ተሽከርካሪ ምዝገባ፣ ባንክ ማረጋገጫ፣ ክምችት፣ ቦንድ፣ የህይወት ኢንሹራን ፖሊሲዎች
- የልጅ ማሳደግ ወይም የጧሪነት ወጪ ማረጋገጫ እንደ ከአቅራቢ ደረሰኝ ያሉ ነገሮች
- የመኖሪያ ቤት ወጪ እንደ የሞርገጅ ክፍያ፣የንብረት ግብር ክፍያ፣ የቤት ባለበትነት ኢንሹራንስ፣ የክራይ ደረሰኝ፣ የሊዝ ኮፒዎ፣ የአገልግሎት ቢሎች፣ ደብዳቤ ከአከራዮችዎ
- ሌሎች ማረጋገጫዎች እንደ ያልተከፈሉ የህክምና ቢሎች፣ የጤና ኢንሹራን ፕሪሚዬም፣ ስለስደትዎ ወይም የዜግንት ሁኔታዎ የሆኑ ለውጦች፣ ጊዜው የተቃረበ እርግዝና፣ የጉድፈቻ ድጋፍ ወይም የክብካቤ ክፊያዎች

ይችላሉ:

- በ www.washingtonconnection.orgለጥቅማጥቅም ያመልክቱ፣ ለእይታ ያስገቡ፣ ወይም ለውጦችን ሪፖርት ያድርጉ
- በ 888-338-7410 መረጃን ፋክስ ያድርጉልን

በላኩልን ሁሉም ኮፒዎች ላይ የደንበኛ መታወቂያ ይጻፉ። የደንበኛዎ መታወቂያ .

ዎርክፈርስት ኬዝ ማናጀርን ወይም ሶሻል ዎርከርን ለማግኘት በ Phone Number (include area c .

ማመልከቻን ወይም እንደገና ማየትን፣ ለዉጦችን ሪፖርት ለማድረግ ወይም ጥያቄዎችን ለመጠየው በ 877-501-2233 ይደውሉ።

ስለዚህ ዴብዳቤ ጥያቄዎችን ካለዎት እባከዎን ይደውሉ።

የተያያዙ አባሪዎች: DSHS 14-113 የደንበኛ መብትና ግዴታዎች

Washington State Department of Social & Health Services
Transforming lives

# የእርስዎ የጥሬ ገንዘብ እና የምግብ ድጎማ መብቶች እና ግዴታዎች

## Your Cash and Food Assistance Rights and Responsibilities

| የደንበኛው ስም (የቤተሰብ ኃላፊ) |
|---|
| የደንበኛው መታወቂያ ቁጥር |

### የእርስዎ ግዴታዎች (የሚከተለውን ማድረግ አለብዎት)

- **ብቁ መሆንዎን ለመወሰን እንድንችል የምንፈልገውን መረጃ ይስጡን።**
- **አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማስረጃ ይስጡን።** እኛ ለእርስዎ ልናገኝልዎት እንችል ይሆናል። ለመምሪያው የሚሰጡት መረጃ በፌደራል እና የስቴት ባለሥልጣናት ትክክለኛነቱ ሊጣራ ይችላል። ማጣራቱ የማጭበርበር ድርጊት መርማሪዎችን ጨምሮ በመምሪያው ሠራተኞች የሚደረግ የክትትል ግንኙነትን ሊያካትት ይችላል።
- **ለማህበራዊ እና ጤና አገልግሎቶች መመሪያ ሪፖርት የተደረገ መረጃ** በጤና ጥበቃ ባለሥልጣን (Health Care Authority) እና በጤና ጥቅም ኤክስቼንጅ (Health Benefit Exchange) አማካይነት ለሚተዳደረው የጤና እንክብካቤ የመድን ሽፋን ላይ በሚኖር ብቁነት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፍ ይችላል።
- **ለውጦችን ያሳውቁ** (ለምሳሌ አድራሻ፣ ገቢ፣ ወዘተ) በሕግ አንቀጽ WAC 388-418-0005 በተደነገገው መሠረት። በሚቀጥለው ወር 10ኛው ቀን በፊት ሪፖርት ያድርጉዋቸው።
- የTANF ድጎማ የሚያገኙ ከሆነ **ከልጅ ድጋፍ ዲቪዝዮን (Division of Child Support (DCS)) ጋር ይተባበሩ።** DCS የልጅ ድጋፍን በእርስዎ እንክብካቤ ሥር ላሉ ሕፃናት እንዲያቋቁም፣ እንዲያሻሽል ወይም እንዲያስፈጽም እንዲሁም (አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ) ወላጅነትን እንዲያሳምን ማገዝ አለብዎት። ከDCS ጋር መተባበሩ እርስዎን፣ የእርስዎን ልጆች፣ ወይም በእርስዎ እንክባካቤ ሥር ባሉት ልጆች ላይ አሳዳጊ ያልሆነው ወላጅ ጉዳት ሊደርስባችሁ እንደሚችል ለማመን በቂ ምክንያት እንዳልዎት ማስረጃ ማቅረብ ከቻሉ ከ DCS ጋር አልተባበርም ማለት ይችላሉ።
- የጥሬ ገንዘብ ድጎማ በሚጠይቁበት ወይም በሚቀበሉበት ጊዜ ከሌሎች ምንጮች ገቢ ለማግኘት **ያመልክቱ** እንዲሁም በቂ ጥረት ያድርጉ።
- **እንዲያቀርቡ የተጠየቁዋቸውን ሪፖርቶች እና ግምገማች ያሟሉ።**
- ለጥሬ ገንዘብ እና ለምግብ ድጎማ **የሥራ መመዘኛዎችን ይከተሉ።**
- በእርስዎ ምትክ ሌላ ሰው የእርስዎን የምግብ ድጎማ እንዲጠቀምበት የሚፈልጉ ከሆነ **ለእኛ ይንገሩን።**
- **ከእኛ የጥራት ቁጥጥር ገምጋሚዎች ጋር ይተባበሩ።**
- **የምግብ ድጎማን** ለቤተሰብዎችዎ አባላት ምግብ ለመግዛት ብቻ **ይጠቀሙበት።**
- **የጥሬ ገንዘብ ድጎማን** ለቤተሰብዎችዎ አባላት ጥቅም ብቻ **ይጠቀሙበት።**
- ድጎማ ለማግኘት ለሚያመለክቱ ሰዎች ብቻ **የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር Social Security Numbers** (SSN) ወይም የኢሚግሬሽን አቋም **ማቅረብ ይኖርብዎታል።** SSNዎች ወይም የኢሚግሬሽን አቋም ማመልከቻ ለማያስገቡ አባላት አለመስጠትን ከመረጡ፣ ሁሉም የቤተሰብ አባላት ገቢዎች እና የገቢ ምንጮች ብቁነትን ለማረጋገጥ አሁንም ቢሆን አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ መጣራት ይኖባቸዋል።

### የእርስዎ መብቶች (እኛ የሚከተለውን ማድረግ አለብን)

- **ማመልከቻ** ከእርስዎ ስም፣ አድራሻ፣ እና ፊርማ ወይም የእርስዎ ሕጋዊ ወኪል ፊርማ ጋር **መቀበል።**
- **የDSHS ቅጾችን እንዲሞሉ እርስዎን ማገዝ።**
- ፈጣን አገልግሎት ለማግኘት ብቁ ሆነው ከተገኙ የእርስዎን የምግብ ድጎማ ጥያቄ በ 7 ቀናት ውስጥ **ማስጀመር።**
- ሰነዶችን በሚሰጡበት ጊዜ ደረሰኝ እንዲሰጥዎት ከጠየቁ **ለእርስዎ ደረሰኝ መስጠት።**
- በአብዛኛው ጊዜ፣ በ30 ቀናት ውስጥ የጽሑፍ ውሳኔ ለእርስዎ መስጠት።
- ከፀረ-ማጭበርበር እና ተጠያቂነት ቢሮ (Office of Fraud and Accountability) የሚመጣውን **የማጭበርበር ድርጊት በጅማሬው ምርመራ (Fraud Early Detection (FRED))** መርማሪ አላናግርም ማለት ይችላሉ። መርማሪው ወደ ቤትዎ እንዲገባ እንዲፈቅዱ አይገደዱም። መርማሪውን በሌላ ጊዜ እንዲመጣ ሊጠይቁት ይችላሉ። ይህ ድጎማ ለማግኘት ባልዎት ብቁነት ላይ ምንም ተጽዕኖ አይኖረውም።
- መምሪያው በእርስዎ ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሳኔ የማይስማሙ ከሆነ **አስተዳደራዊ ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲቋቋምልዎት መጠየቅ ይችላሉ።** አስተዳደራዊ ይግባኝ ሰሚ ችሎት እንዲቋቋምልዎት የመጠየቅ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ የሥራ የበላይ ኃላፊ ወይም አስተዳዳሪ ካለመግባባት ላይ ያደረሰውን ውሳኔ ወይም እርምጃ እንዲገመግመው ሊጠይቁ ይችላሉ።
- ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጎማ (Temporary Assistance for Needy Families (TANF)) መርሃግብር ሥር ስላለው የ60-ወራት የጊዜ ገደብ **ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን።** ይህ የጊዜ ገደብ በእርስዎ የመሠረታዊ ምግብ፣ ወይም የልጅ እንክብካቤ ድጎማዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

### ስለየእርስዎ EBT ካርድ ማወቅ ያሉብዎት ነገሮች

- **የጥቅማጥቅሞች አላግባብ መጠቀም፦** በEBT ካርድ አማካኝነት የተወሰዱ የምግብ እና የጥሬ ገንዘብ ጥቅማጥቅሞች እርስዎ የት ቦታ ጥቅማጥቅሞችዎን እንደተጠቀሙባቸው የሚገልጽ የግብይት ታሪክ ለDSHS ይሰጣሉ። መምሪያው የግብይት መረጃን የጥሬ ገንዘብ ድጎማ ጥቅማጥቅሞችን አላግባብ መጠቀምን ወይም የምግብ ድጎማ ጥቅማጥቅሞችን በጥሬ ገንዘብ ወይም ሌላ የገንዘብ ዋጋ ያላቸው (ሕገወጥ ዝውውር) የመሳሰሉ ልውውጦች መደረጋቸውን ለማጣራት በሚደረጉ ምርመራዎች ላይ ይጠቀምበታል።
- **የEBT ካርድ ምትክ ማግኘት፦** የEBT ካርዶች ምትክ ለመስጠት ገንዘብ ልናስከፍል እንችል ይሆናል። የእርስዎን EBT ካርድ እና የግል መለያ ቁጥር (personal identification number (PIN)) ደህንነቱ በተጠበቀ እና በአስተማማኝ ቦታ ይያዙዋቸው።
- **ከፍተኛ ቀሪ ሒሳብ ያላቸው EBT ካርዶች፦** በአንድ ጊዜ ለበርካታ ወራት ጥቅማጥቅሞችዎን ሳይጠቀሙባቸው ከቀሩ ወይም ከበርካታ ወራት በኋላ ከፍተኛ ቀሪ ሒሳብ ካጠራቀሙ፣ ያሉበትን አቋም ለመገምገም ወይም ጥቅማጥቅሞቹን ያስፈልግዎት እንደሆነ ለማወቅ አግኝተን እናነጋግርዎታለን።

## ማወቅ ያለቡዎት ነገሮች (መሠረታዊ ምግብ)

- የተሰጠው መረጃ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ለመሠረታዊ ምግብ ስለሚያመለክቱ ሰዎች **መረጃ** ወደ ሌሎች የፌደራል ኤጀንሲዎች **እንልካለን።** መረጃው ትክክል ሆኖ ካልተገኘ ማመልከቻ ያቀረቡት ሰዎች መሠረታዊ ምግብ ላያገኙ ይችላሉ። አንድ ግለሰብ የሰጠው መረጃ ትክክለኛ እንዳልሆነ እያወቀ መረጃውን ከሰጠ በወንጀል ተከሶ ሊጠየቅ ይችላል። የመሠረታዊ ምግብ ደንቦችን ሆን ብሎ መጣስ ከመርሃግብሩ መሰረዝ ጀምሮ እስከ ገንዘብ ቅጣት ወይም እስር ድረስ ሊለያይ የሚችል ቅጣቶችን ያስከትላል።
- ለማናቸውም በገንዘብ ሊመነዘር የሚችል እንደ ጥሬ ገንዘብ፣ አደገኛ መድሃኒት፣ የጦር መሣሪያዎች ወይም ከምግብ ውጭ ለሆነ ማናቸውም ሌላ ነገር ከተፈቀደለት አከፋፋይ ውጭ (ሕገወጥ ዝውውር) **የምግብ ድጎማዎን ከሸጡ፣ ለመሸጥ ከሞከሩ፣ ከተለዋወጡበት ወይም በስጦታ ከሰጡት** የምግብ ድጎማን እንዳያገኙ በትንሹ ለአንድ ዓመት ገፋ ቢል ለዕድሜ ዘመን በሙሉ በመጀመሪያው ጥፋት ሊታገዱ ይችላሉ። ይህ እገዳ የዋሽንግተን ስቴትን ለቀው ቢሄዱ እና ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት በሌላ ስቴት በሚያመለክቱበት ጊዜም እንደጸና ይቀጥላል።
- **በመሠረታዊ የምግብ ለሥራ መመዘኛዎች እንዲሳተፉ ከተጠየቁ፣** እና ሳይሳተፉ ቢቀሩ፣ በሥራ መሥራት መመዘኛው ግዴታ እስከሚገዙ ድረስ ከመጀመሪያው ስህተትዎ ጀምሮ እስከ አንድ ወር ለሚደርስ ጊዜ ሊታገዱ ይችላሉ፣ ለሁለተኛ ጥፋት በግዴታው እስከሚገዙ ለሶስት ወራት፣ ለሶስተኛ ጥፋት በግዴታው እስከሚገዙ ድረስ ለስድስት ወራት እና ከዚህ በኋላ ባጠፉ ቁጥር ለስድስት ወራት ሊታገዱ ይችላሉ።
- **ከመሠረታዊ ምግብ መርሃ ግብር** በዚህ ገጽ ላይ በተዘረዘረው የመሠረታዊ ምግብ ቅጣት ማስጠንቀቂያ ገጽ ላይ በተዘረዘረው መሠረት የመሠረታዊ ምግብ መርሃ ግብርን ደንቦች በመጣስ **ሊወገዱ ይችላሉ።**
- ***መምሪያው የቤት ወጪዎችን ወደ መሠረታዊ ምግብ እንዲያካትታቸው ከፈለጉ የቤት ወጪዎችን መጠን ሪፖርት ያድርጉ።*** *ሪፖርት ካላደረጉ እና የእነዚን ወጪዎች ማስረጃ ሳያቀርቡ ቢቀሩ፣ ተጨማሪ መሠረታዊ ምግብ ድጎማ እንዲያገኙ እነዚህን ወጪዎች እንዳናካትታቸው እየነገሩን ነው ማለት ነው።*

## ማወቅ ያሉብዎ ነገሮች (ጥሬ ገንዘብ)

- **ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ ድጎማ** (Temporary Assistance for Needy Families (TANF)) **በማግኘት** የእርስዎን የልጅዎን እና የባለትዳርነት መብቶች አሳልፈው ለልጅ ድጋፍ ዲቪዝዮን ይሰጣሉ። ይህ ማለት DCS ከሕዝባዊ ድጎማው ያገኙት ገንዘብ ያክል ለእርስዎ መሰጠት ያለብትን ድጎማ አስቀርቶ ሊይዝ ይችላል ማለት ነው። በTANF ልጅዎ በሚቆይበት ጊዜ **የልጅ ድጋፍ ክፍያዎችን ካገኙ ወዲያውኑ ለDCS ማሳወቅ አለብዎት።**
- TANF **ማግኘትዎ ከቆመ** የእርስዎን የልጅ ድጋፍ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳርፍ ማናቸውም ለውጥ ከተፈጠረ እንደ ልጁ አድራሻ ከለወጠ ወይም የእርስዎ አድራሻ ከተለወጠ ለDCS ማሳወቅ ይኖርብዎታል።
- TANF **የሚቀበሉ ከሆነ** ጊዜያዊ ድንገተኛ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ወጪዎችን ለመክፈል እንዲችሉ እንዲያግዝዎት **ተጨማሪ ትርፍ ገንዘብ እንዲሰጥዎት መጠየቅ ይችላሉ።**

በፌደራል ዜጎች መብት ሕግ እና በአሜሪካ የእርሻ ሚኒስቴር (Department of Agriculture (USDA) ሰባዊ መብት ደንቦች እና ፖሊሲዎች USDA እና ኤጀንሲዎቹ ጽ/ቤቶች እና ሠራተኞች እንደዚሁም በ USDA የሚሳተፉ ወይም ፕሮግራሙን የሚያስተዳድሩበዘር፣ በቀለም፣ በብሔራዊ የቀድሞ ማንነት፣ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ በፆታ ማንነት፣ (ፆታዊ መገለጫዎችን ጨምሮ)፣ ፆታዊ ፍላጎቶችን፣ አካል ጉዳተኝነት፣ ዕድሜ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቤተሰብ ሁኔታ፣ ከሕዝብ ድጋፍ በሚገኘው ገቢ ፕሮግራም፣ የፖለቲካ አመለካከት ወይም ቀድሞ ለነበረው ሰብአዊ መብቶች እንቅስቃሴ መበቀል በማንኛውም በUSDA ፕሮግራም ወይም የተከወነ ነገር ወይም ገንዘብ የተደገፈ (ሁሉም መነሻዎች ለሁሉም ፕሮግራመሞች አይሰራም). መፍተንና ቅረታን ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ በፕሮግራም ይለያያል፡፡

ለፕሮግራሙ መረጃ አማራጭ ኮሙንከሽን መንገድን ለምፈልጉ አካል ጉዳተኞች (ለምሳሌ ብሬል፣ ትላልቅ ፍደላት፣ ድምጽ ማጫወቻ፣ የአመርካ የምልክት ቋንቋ ወዘተ.) የሚመለከተውን ኤጀንሲ ወይም USDA’s TARGET ማዕከልን በ(202) 720-2600 (ድምጽ እና TTY) ወይም USDAን በ ፌደራል ሪሌይ አገልግሎትን በ (800) 877-8339 ማግኘት፡፡ በተጨማሪ የፕሮግራሙ መረጃ ከእንግሊዝኛ ውጪ በሌሎች ቋንቋ መቅረብ ይችላል፡፡

የፕሮግራሙ አድሎ ቅረታን ለማቅረብ በ AD-3027, አንላይን በ http://www.ascr.usda.gov/complaint_filing_cust.html እና በማንኛውም የUSDA ጽ/ቤት ወይም USDA ፕሮግራም አድሎ ቅሬታ ቅፅን መሙላት ወይም ለUSDA ዴብዳቤ መጻፍና መቅጹ የተቀመጠውን መረጃ ማቅረብ፡፡ የቅሬታ ማቅረቢያ ቅፅ ኮፒ ለማግኘት በ (866) 632-9992 ይደውሉ፡፡ የሞሉትን ቅጽ ወይም ደብዳቤ ለ USDA ለመላክ፡

1. ለ በአሜሪካ የእርሻ ሚኒስቴር U.S. Department of Agriculture
   Office of the Assistant Secretary for Civil Rights
   1400 Independence Ave, SW
   Washington, D.C. 20250-9410;
1. ለ (202) 690-7442; ፋክስ ያድርጉ ወይም
2. ለ program.intake@usda.gov ኢ-ሜይል ይላኩ

USDA እኩል የሆነ የአቅርቦት፣ ቅጥር እና ብድር ዕድሎችን ያቀርባል፡፡.

USDA ለሁሉም እኩል ዕድል የሚሰጡ አገልግሎት አቅራቢዎች እና ቀጣሪዎች ናቸው።

ከዚህ በታች በመፈረም ከDSHS ጥቅማጥቅሞችን እና መርሃ ግብሮችን በመቀበል ረገድ ያሉኝ መብቶች እና ያሉብኝ ግዴታዎች ምን እንደሆኑ ለእኔ እንደተብራሩልኝ አረጋግጣለሁ። ይህን ሰነድ አልፈርምም ብል የእኔ ብቁነት ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ባይኖርም በመርሃ ግብር መመዘኛዎች ተጠያቂ እንደምሆን እና ተፈጻሚነት በሚኖራቸው የመርሃግብሩ ወይም የወንጀል ቅጣቶች ተጠያቂ እንደምሆን ተረድቼያለሁ።

| የአመልካች ፊርማ | ቀን | አብሮ አመልካች ፊርማቀን |
|---|---|---|
| | | |

የDSHS ሠራተኛ ACES መታወቂያ፡-

☐ አልፈርምም ብለዋል።